# “ላለፈዉ ይቅር ይበላችሁ ለሚመጣውም ይጠብቃችሁ”

ጥንታዊቷ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ለረጅም ዓመታት ያህል ከኮብቲክ ( ግብፅ) ጳጳሳትን እያመጣች በግብፅ ቀንበር ስር ወድቃ ዘመናትን ማሳለፏ ዕዉን ነው። በራሷ ልጆች መተዳደር ከጀመረች እነሆ 48 ዓመታትን አስቆጥራለች።

የመጀመሪያዉ ፓትርያርክ አቡነ ባስልዩስ ለ11 ዓመታት ፤ ቀጥሎ አቡነ ቴዎፍሎስ ለ4 ዓመታት፤ አቡነ ተክለ ኃይማኖት ለ12 ዓመታት፤ አቡነ መርቆሬዎስ በመንበራቸዉ ላይ ለ3 ዓመታት በስደት 18 ዓመታት አስቆጥረዋል። በዚህ ዘመኗ ቤተክርስቲያኗ ልትሸከመዉ የማትችል ከባድ ፈተናዎች ተፈራርቀዉባታል።  የደርግ መንግስት ፓትርያርኳን አስሮ ገድሎባታል። የወያኔ መንግስት ፓትርያርኳን አውርዶ መንበሯን ደፍሮ ሕገ ወጡን አባ ገ/ መድህንን አስቀምጦ ለዉርደት ዳርጓታል።

ቤተክርስቲያኗ ይህንን የመሳሰሉ ፈተናዎች እየተፈራረቁባት ትገኛለች። 4ተኛዉ ፓትርያርክ ምንም እንኳን ስደት መራራ አስቸጋሪ ፈታኝ ቢሆንባቸዉም በስደቱ ዓለም ብዙ መንፈሳዊ ስራዎችን ሰርተዋል። ከሰሯቸዉ ስራዎች ውስጥ አብያተክርስቲያናትን አስፋፍተዋል፤ ለሀገርና ለሕዝብ ጠቃሚ የሆኑ መንፈሳዊ መልእክቶችን አስተላልፈዋል፤ ጳጳሳትን ሾመዋል ከተሿሚዎች ውስጥ በመንፈሳዊነታቸዉ፤ በእዉቀታቸዉ እጅግ ቤተክርስቲያንን የሚጠቅሙና እየጠቀሙ ያሉ ብዙ ናቸው። በሌላ በኩል በመልካም ሰብል ላይ እንክርዳድ መድፋት ባህሪው የሆነው ርጉም መንፈስ **ባባትነት የተቀመጡትን** ትክክለኛ መንፈሳዊ አቅጣጫ ይዘው እንዳይጓዙ እያደረገ ነው።

አባ ሳዊሮስ ሦስቱን አብያተክርስቲያናት በሳዉዝ ዳኮታ፤ በሚኒሶታን እና በደንቨርን እየተዘዋወሩ እንዲባርኩ በብፅዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ አንብሮተ ዕድ ተሹመዋል። መቀመጫቸውም ሚኒሶታ ሆኖ ሳለ በአባ ሲራክ ፍላጐት ወደ ደንቨር መጥተው መኖር ከጀመሩ 4 ዓመት ሆኗቸዋል። እኛም ክርስቲያኖች አባ ሲራክን አመሰገን ጳጳስ ከጐናችን ሆነ ብለን እጅግ ደስ ብሎን ፍቅርን መንፈሳዊ ስጦታን ሊያበዙልን ነው ብለን በብዙ ተስፋ አድርገን ነበር። **“ጉድና ጅራት ወደኋላ”** እንዲሉ እየቆየን ስንሄድ ግን ሁሉም ከንቱ መና ሆነ  ጳጳሱ ፍፁም ቤተክርስቲያኗን ከሚጐዱ ክፍሎች ጋር በመሆን ባንድነት ፋንታ መለያየትን፤ በፍቅር ፋንታ መጠላላትን፤ በበረከት ፋንታ መርገምን እንዲሰፍን አደረጉ።

አቡነ ሳዊሮስ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ እጅ የኤጲስ ቆጶስ ማዕረግ ሲቀበሉ “ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን እጠብቃለሁ አስጠብቃለሁ” ወዘተርፈ ብዙ ብዙ ቃለ መህላ ፈፅመው ነበር። ሆኖም ግን ቃላቸውን  አልጠበቁም ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን አላከበሩም አላስከበሩም።

ለእግዚአብሔር መንጋ የማይራሩ ጨካኝ ተኩላዎች በቦታው ስለተነሱ ጥንቃቄ የተሞላበት መንጋ የመታደግ አገልግሎት ያስፈልጋል። የሐዋርያው ማስጠንቀቂያ ይህ ነበር “በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔር ቤተክርስትያን ትጠብቋት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጐ ለሾመባት ለመንጋው ሁሉና  ለራሳችሁ ተጠንቀቁ ከኔ በኋላ ለመንጋይቱ የማይራሩ ነጣቂዎች ተኩላዎች እንደሚመጡ እኔ አውቃለሁ”  ※ የሐ. ሥራ .  20 ፡- 28 – 30

ይህ ከላይ የሰፈረው የሐዋርያው ማስጠንቀቂያ እጅግ ከባድ ሆኖ ሳለ አባ ሳዊሮስ አንዱንም አልፈፀሙትም።  በዚህ ቤተክርስቲያን ሕግና ሥርዓት ሲፈርስ ፍርድ ሲጓደል ብፁአን አባቶች ሲሰደቡ

በቦታው ላይ ቁጭ ብለው አንድ ቃል ሳይተነፍሱ የወር ቀለባቸውን ብቻ እየተቀበሉ **ጀሮ ዳባ** ልበስ ማለታቸው ብዙኃኑን አስለቅሷል። ይምጡ አብረን እንኑር ያለን ወንድም በግፈኞች እጅ ግፍና በደል ሲደርስበት ይልቁንም የበዳዮች ተባባሪ ሆነው በመገኘታቸው እኛን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን አማኞች በጵጵስናቸውና በአባትነታቸው እንድናፍር አድርጉናል።

አቡነ ሳዊሮስ አሜሪካን ሀገር በሦስት የተለያዩ ቦታዎች ማለትም በካሊፎርኒያ፤ ሚኒሶታ እንደኖሩ ይነገርላቸዋል። በኖሩባቸው ቦታዎች ሁሉ ፍቅረ ቢፅ የሌላቸው ሁከት ፈጣሪ እንደሆኑ በሰፊው ይነገራል በነዚህ ከላይ በተጠቀሱት ቦታዎች እጅግ አስከፊና አሳዛኝ ተግባርን ፈፅመው እንዳለፉ በሰፊው ይወራል። አሁን ደግሞ በደንቨር ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን የተፈጠረውን ችግር በተሰጣቸው የጵጵስና ሥልጣን ተጠቅመው መፍታት ሲገባቸው ችግር ፈጣሪ የአድማ መሪ ሆኖ መገኘት ባልተገባም ነበር። በቤተክርስቲያኗ ላይ ወደፊት ለሚደርሰው አላስፈላጊ ችግር አባ ሳዊሮስ ከተጠያቂነት ነፃ አይደሉም።

" ለዘኃለፈ ሥርየት ወለዘይመጽእ እቅበት" ሥርየት የማይፈታው ችግር የለም ነገሮች አንድ ቦታ ላይ እንደሚጀመሩ ሁሉ አንድ ቦታ ላይም ሊቆሙ ይችላሉ። ጥፋትና በደል ከአዳም አባታችን ጀምሮ አለ ሁልጊዜም የሚፈታው በይቅርታና በሥርየት ነው። ሊቀ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስ " ጌታ ሆይ ወንድሜ ቢበድለኝ ስንት ጊዜ ልተዉለት እስከ ሰባት ጊዜን? ባለው ጊዜ ጌታ፡- እስከ ሰባ ጊዜ ሰባት እንጂ እስከ ሰባት ጊዜ አልልህም" ያለው ይቅርታና ሥርየት በቁጥርና በጊዜ የማይወሰን ሁልጊዜም የሚፈፀም በመሆኑ ነው። ስለዚህ አሁንም ለውይይትና ለሥርየት ጊዜ አለ። ልዩነቶችን ውይይት ያቆማቸዋል ይቅርታ ይፈታቸዋል ሥርየትም ባንድነት ያፀናቸዋል ይልቁንም ደግሞ በቤተክርስቲያን ዉስጥ ያለን ችግር ያለ ሥርየት ልንፈታው አንችልም **ሥርየትን ኑዛዜ፤ ኑዛዜንም ዉይይት** ይቀድማቸዋል **ውይይት ከሁሉም ይቅደም።** ስለዚህ እንደ ፀሎታችን እንደ ዕለት ተዕለት ሕይወታችን ያለፈውን በይቅርታ ፈትተን ለሚመጣው ደግሞ ችግሮቻችን የምንፈታባቸውን መንገዶች ቀይሰን ወደ አንድነታችን መፍጠን ይጠበቅብናል። ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ ሆይ ሲናዝዙን የምንሰማው **ጨዋነቱ ባያሳስተኝ** " ለዘኃለፈ ሥርየት ወለዘይመጽእ እቅበት" "ላለፈዉ ይቅር ይበላችሁ ለሚመጣውም ይጠብቃችሁ" ይሉ የለ? ይህን ችግር ሲተገበሩ ማየት ሁሉም ይጠብቃልና ።

ወደፊት በሰፊው እስክንገናኝ ቸር ይግጠመን

ከደንቨር ዳግማዊት ግሸን ቅ/ማርያም ምዕመናን

**አሣዩ ዕዉነቱ**